# የእግዚአብሔር ኃይል



**የማይሸጥ**

# የእግዚአብሔር ኃይል

## በዋትሰን ጉድማን የተቀነባበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች
## የማይሸጥ ፥ በነፃ የሚታደል
## የእግዚአብሔር ኃይል

አንድ በጣም አነስተኛ የሆነ ሚች ሰው ችሎታው በሁሉ ነገር መጨረሻ የሌለውን የአምላካችንን ኃያልነት እንዴት አድርጎ መግለጥ ይችላል ? እግዚአብሔር በጣም ኃያልና ታላቅ እንዲሁም ወሰን የሌለው ስለሆነ የእኛ ትንሽ አእምሮ ባላት ችሎታ ሁሉ እርሱን ታስገባለች ማለት ዘበት ነው ።

ለሰው የማይቻለውን ነገር እግዚአብሔር በማይወሰን ችሎታው ሁሉን ነገር ማድረግ እንደሚችል የራሱ መጽሐፍ በሆነው ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ፤ ራሱን በመግለጥ በቂ ማስረጃ ሰጥቶአል! እርሱ ይህችን አለማችንን ፈጥሮ በኅዋው ውስጥ አንጠልጥሎአታል ፥ እርስዋም በኅዋው ውስጥ ከተንጠለጠለች ብዙ ሺህ ዘመናት ያለፉዋት ሲሆን በዚያ ስፍራ ጸንታ የቆመችው በሌላ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ደጋፊነት ኃይል ነው ። እርሱም ሁለቱም ማለት ሰውና ሰይጣን ምድርን እንዳያጠፉበት በሚያስፈልጋት ነገር አሚልቷት ነበር ።

እስቲ ጨርሶ ስለማይወሰነው ችሎታው የሚገልጸውን ክፍል ፤ ከእግዚአብሔር ቃል አንድ ጊዜ እንመልከት ።

## ፩. የእግዚአብሔር የመፍጠር ኃይል

ኤርሚያስ ፲ ፡ ፲፪

ምድርን በኃይሉ የፈጠረ ፣ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እሱ ነው።

ኢሳ. ፵ ፡ ፲፰ ፤ ፳፪ ፳፭ ና ፳፮ ።

እንግዲህ እግዚአብሔርን ፣ በማን ትመስሉታላችሁ ? .... እርሱ በምድር ክበብ ላይ ይቀመጣል ፣ በእርስዋም የሚኖሩት እንደ አንበጣ ናቸው ፤ ሰማያትን እንደ መጋረጃ የሚዘረጋቸው እንደ ድንኳንም ለመኖርያ የሚዘረጋቸው ፣ ... እንግዲህ እስተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ ? ይላል ቅዱሱ ። ዓይናችሁን ወደ ላይ አንሥታችሁ ተመልከቱ ፣ እነዚህን የፈጠረ ማን ነው ? ሠራዊታቸውን በቁጥር የሚያወጣ እርሱ ነው ፣ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል ፤ በኃይሉ ብዛትና በችሎቱ ብርታት አንድስ እንኳ አይታጣውም ።

ኤርሚያስ ፴፪ ፡ ፲፯

አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፣ እነሆ አንተ ሰማይና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል ፣ ለአንተም የሚያቅት ነገር የለም ።

ዕብራውያን ፩ ፡ ፩ ና ፪

ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር .... ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን ።

፩. ሰይጣን ከዋክብትን ፈጥሮ በጎዋ ውስጥ ማን ጠልጠል አይችልም ።

የሐንስ ፩፡፩ና ፫ ፤ ፲ ፡ ፲

በመጀመሪያው ቃል ነበረ ፡ ቃልም በእግዚ አብሔር ዘንድ ነበረ ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ... ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም ። ... ሌባው ሊያርድ ሊያ ጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም ፤ .....

ሉ ስ ፲ ፡ ፲፰

እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ ።

፩ኛ ጴጥሮስ ፭ ፡ ፰

በመጠን ኑሩ ንቁም ፣ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞ ራልና ።

የሐዋርያት ሥራ ፲፯ ፡ ፳፱

እንግዲህ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከሆንን ፡ አምላክ በሰው ብልሃትና አሃብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፡ ፳

... ከአጋንንትም ጋር ማኅበርተኞች እንድትሆኑ አልወድም ።

የሐንስ ፰ ፡ ፲፪

ደግሞም ኢየሱስ ፡—እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።

## ፫. የእግዚአብሔር ኃይል ድንበር የለውም ።

መዝሙር ፷፩ ፡ ፲፩

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ ፥ እኔም ይህን ብቻ ሰማሁ ፤ ኃይል የእግዚአብሔር ነው ።

መዝሙር ፻፲፫ ፡ ፲፩

አምላካችንስ በላይ በሰማይ ነው ፤ በሰማይም በምድርም የፈቀደውን ሁሉ አደረገ ።

ኢሳያስ ፵፫ ፡ ፲፫

ከጥንት ጀምሮ እኔ ነኝ ከእጄም የሚያመልጥ የለም ፤ ...

ዜና መዋዕል ፳፱ ፡ ፲፩ ና ፲፪

አቤቱ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል ፥ ክብርም ፥ ድልና ግርማ ለአንተ ነው ፤ አቤቱ መንግሥት የአንተ ነው ፥ አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ ። ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው ፥ አንተም ሁሉን ትገዛለህ ፤ ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው።

ዘዳግም ፫ ፡ ፳፬

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፥ ታላቅነትህን የጸናችውንም እጅህን ለእኔ ለባሪያህ ማሳየት ጀምረሃል ፤ በሰማይና በምድርም እንደ ሥራህ እንደ ኃይልህም ይሠራ ዘንድ የሚችል አምላክ ማን ነው ?

ሉቃስ ፩ ፡ ፴፯

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ።

## ፬. መጨረሻ የሌለው የእግዚአብሔር ኃይል ታላቅነት

ዘጸአት ፲፭ ፡ ፯

በክብርህም ብዛት የተነሡብህን አጠፋህ ፥ ቁጣህን ሰደድህ ፥ እንደ ገለባም በላቸው ።

መዝሙር ፻፵፯ ፡ ፭

ጌታችን ታላቅ ነው ፤ ኃይሉም ታላቅ ነው ፤ ለጥበቡም ቁጥር የለውም ።

መዝሙር ፻፮ ፡ ፰

ኃይሉን ግን ለማስታወቅ ስለ ስሙ አዳናቸው።

ነህምያ ፱ ፡ ፮

አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ ፤ ሰማዩንና የሰማያት ሰማይን ሠራዊታቸውንም ሁሉ ፥ ባሕሮቹንና በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ፈጥረሃል፥

ነፍሴ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ ፤ አቤቱ አምላኬ ሆይ አንተ እጅግ ታላቅ ነህ ፤ ክብርንና ግርማን ለበስህ ።

መዝሙር ፻፵፭ ፡ ፪ ና ፫

በየቀኑ ሁሉ እባርክሃለሁ ፥ ስምህንም ለዘላለም አመሰግናለሁ ። እግዚአብሔር ታላቅ ነው እጅግም የተመሰገነ ነው ። ለታላቅነቱም ፍጻሜ የለውም ።

ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል ፤ የሰማዩም ሠራዊት ለአንተ ይሰግዳሉ ።

## ፫. የእግዚአብሔር ኃይል ዘለዓለማዊ ነው።

፪ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፲፩ ።
እንዲሁ ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና ።

ኢሳይያስ ፳፮ ፡ ፬
ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም አምባ ነውና ለዘላለም በእግዚአብሔር ታመኑ ።

መዝሙር ፺፱ ፡ ፪
ተራሮች ሳይወለዱ ፥ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ ።

ኤርምያስ ፲ ፡ ፲
እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው ፤ እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው ፤ ከቁጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች ፥ አሕዛብም መዓቱን አይችሉም ።

ራዕይ ፲፭ ፡ ፲፫
.. በሰማይም ፡—የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምጾች ሆኑ ።

ራዕይ ፳ ፡ ፲
ያሳታቸው ዲያቢሎስ ... ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ... ይሣቀያል ።

## ፯. በቀይ ባሕር የተደረገው አስፈሪ የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል

ዘፀዓት ፲፬ ፡ ፳፩ ፤ ፳፪ ፤ ፳፮—፳፰ ፤ ፴ ና ፴፩

ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ ፤ እግዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው ፤ ባሕሩንም አደረቀው ፤ ውኃውም ተከፈለ ። የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል በየብስ ገቡ ፤ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው ። .... እግዚአብሔርም ሙሴን ፡—እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ ፤ ውኃውም በግብፃውያን በሰረገሎቻቸውም በፈረሰኞቻቸውም ላይ ይመለስ አለው ። ሙሴም እጁን በባሕሩ ዘረጋ ፤ ባሕሩም ማለዳ ወደ መፍሰሱ ተመለሰ ፤ ግብፃውያንም ከእርሱ ሸሹ ፤ እግዚአብሔርም ግብፃውያንን በባሕሩ መካከል ጣላቸው ። ውኃውም ተመልሶ በኋላቸው ወደ ባሕር የገቡትን ሰረገሎችን ፈረሶችንም የፈርዖንንም ሠራዊት ሁሉ ከደነ ፤ ከእነርሱም አንድ ስንኳ አልቀረም ። .... እግዚአብሔር በዚያ ቀን እስራኤልን እንደዚህ ከግብፃውያን እጅ አዳነ ፤ እስራኤልም የግብፃውያንን ሬሳ በባሕር ዳር አዩ ። እስራኤልም እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያደረጋትን ታላቂቱን እጅ አዩ ። ....

፮. እግዚአብሔርን የሚያቅተው ምንም ዓይነት ተአምራት የለም ።

አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎችን ፵ ዓመት መግቦአል ።

ዘጸአት ፲፮ ፡ ፲፬—፲፭ ና ፴፭

.... ወደ ማታ ሥጋን ትበላላችሁ ፥ ማለዳም እንጀራን ትጠግባላችሁ ፤ እኔም እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ በላቸው ። እንዲህም ሆነ በመሸ ጊዜ ድርጭቶች መጡ ፡ ሰፈሩንም ከደኑት ፤ ማለዳም በሰፈሩ ዙሪያ ጠል ወድቆ ነበር ። የወደቀውም ጠል ባለፈ ጊዜ እነሆ በመሬት ላይ እንደ ደቃቅ ውርጭ ሆኖ ቅርፊት የሚመስል ደቃቅ ነገር በምድረ በዳ ታየ ። የእስራኤልም ልጆች ባዩት ጊዜ ያ ምን እንደሆነ አላወቁምና እርስ በርሳቸው ፡—ይህ ምንድር ነው ? ተባባሉ ። የእስራኤልም ልጆች ወደሚኖሩባት ምድር እስኪመጡ ድረስ አርባ ዓመት መና በሉ ፤...

ለአንድ ሚሊዮን ሰዎች ውኃ

ዘጸአት ፲፯ ፡ ፮

እነሆ እኔ በዚያ በኮሬብ በዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ ፤ ዓለቱንም ትመታለህ ፥ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውኃ ይወጣል አለው ።

የሚፈሰውን ወንዝ አቆመ ።

ኢያሱ ፫ ። ፲፯

የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካከል በደረቅ መሬት ጸንተው ቆመው እስኪሻገሩ ድረስ እስራኤል ሁሉ በደረቅ መሬት ተሻገሩ ።

፰. እግዚአብሔር በጣም ታላቅ የሆነ የሚያስጥል አምላክ ነው ።

ዳንኤል ፫ ፡ ፳፩ ፥ ፳፪ና ፳፯

የዚያን ጊዜም እነዚህ ሰዎች ከሰናፊላቸውና ከቀሚሳቸው ከመጐናጸፊያቸውም ከቀረውም ልብሳቸው ጋር ታስረው በሚነድድ በእቶን እሳት ውስጥ ተጣሉ ። የንጉሡም ትእዛዝ አስቸኳይ ስለሆነ የእቶኑም እሳት እጅግ ስለሚነድድ ሲድራቅ ንና ሚሳቅን አብደናጎንም የጣሉአቸውን ሰዎች የእሳቱ ወላፈን ገደላቸው ። መሳፍንቱና ሹማምንቶቹም አዛዦቹና የንጉሡ አማካሪዎች ተሰብስበው እሳቱ በእነዚያ ሰዎች አካል ላይ ኃይል እንዳልነበረው ፣ የራሳቸውም ጠጉር እንዳልተቃጠለች ፣ ሰናፊላቸውም እንዳልተለወጠ ፣ የእሳቱም ሽታ እንዳልደረሰባቸው አዩ ።

ዳንኤል ፮ ፡ ፲፮ ፥ ፳፩ ና ፳፪

የዚያን ጊዜም ንጉሡ አዘዘ ፥ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጉድጓድ ጣሉት ፥ ንጉሡም ተናገረ ዳንኤልንም ፡— ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ እርሱ ያድንህ አለው ። ... ዳንኤልም ንጉሡን ፡— ንጉሥ ሆይ ፣ ሺህ ዓመት ንገሥ ። በፊቱ ቅንነት ተገኝቶብኛልና ፣ በአንተም ፊት ደግሞ ንጉሥ ሆይ ፣ አልበደልሁምና አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ ፣ እነርሱም አልጐዱኝም አለው ።

## ፱. የእግዚአብሔር ቃል ኃይለኛነት

ኤርምያስ ፳፫ ፡ ፳፱

በውኑ ቃሌ እንደ እሳት ፣ ድንጋዩንም እን ደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለችምን ? ይላል እግዚ አብሔር ።

ዕብራውያን ፬ ፡ ፲፪

የእግዚአዎሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠ ራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተ ሳለ ነው ፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅል ጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል ፣ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል ።

ኤፌሶን ፮ ፡ ፲፯

የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው ።

መዝሙር ፻፲፱ ፡ ፱

ጐልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል ? ቃልህን በመ ጠበቅ ነው ።

ዮሐንስ ፲፭ ፡ ፫

እናንተ ስለነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ ..... ፤

ዮሐንስ ፲፯ ፡ ፲፯

በእውነት ቀድሳቸው ፤ ቃልህ እውነት ነው ።

ፊልጵስዩስ ፪ ፡ ፲፮

የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ ....

ዮሐንስ ፰ ፡ ፴፩

ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ ፡ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ ።

## ፲. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ ነው ።

ቆላስይስ ፪ ፡ ፱

በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና ፤

ማቴዎስ ፩ ፡ ፳፫—፳፭

እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል .... ትርጓሜውም ፡— እግዚአብሔር ከኛ ጋር የሚል ነው ። ዮሴፍም ... የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው ።

ዮሐንስ ፭ ፡ ፲፯ ና ፲፰

ኢየሱስ ግን ፡— አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው ። እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም ፥ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ ፡— እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር ።

ሮሜ ፩ ፡ ፬

እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ... ተገለጠ .... ።

የክርስቶስ ደም የእግዚአብሔር ደም ነው።

የሐዋርያት ሥራ ፳ ፡ ፳፰

በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ።

## ፲፩. ኢየሱስ ክርስቶስ ኃያል ነው ።

ራዕይ ፩ ፡ ፳ና ፰

ከኢየሱስ ክርስቶስ ... ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ ፡— አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል ።

ቆላስይስ ፩ ፡ ፲፫—፲፯

እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን ፣ ቤዛነቱ ንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን ። እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው ፤ የሚታዩትና የማ ይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮ አል ።

፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮ ፲፬—፲፮

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ያለ እድፍና ያለ ነቀፋ ሆነህ ትእዛዙን ጠብቅ ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ ፣ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ያሳ ያል ። እርሱ ብቻ የማይሞት ነው ። .... ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን አሜን ።

ሮሜ ፰ ፡ ፴፭ ና ፴፯

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ? መከራ ወይስ ጭንቀት ፡ ወይስ ስደት ፡ ወይስ ራብ ፣ ወይስ ራቁትነት ፡ ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ።

## ፲፬. ኢየሱስ ከአብ ጋር የበላይ ነው ።

ዮሐንስ ፲፬ ፡ ፱
እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል ።

ዕብራውያን ፩ ፡ ፫
እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ፥ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ ።

ኤፌሶን ፩ ፡ ፲፱—፳፪
ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው ፤ ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሊያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል ፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ....... ።

ዮሐንስ ፲ ፡ ፴ ና ፴፰
እኔና አብ አንድ ነን ። .... ባደርገው ግን ፥ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ ።

ዮሐንስ ፭ ፡ ፳፯
የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው ።

## ፲፫. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል

**እርሱ ከሥላሴዎች አንዱ የሆነ ኃያል ነው።**

፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፡ ፰

የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና ፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ ።

የሐዋርያት ሥራ ፭ ፡ ፫—፭

ጴጥሮስም ፡— ሐናንያ ሆይ ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ ? ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን ? ከሸጥሽውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን ? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው ። ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ ሞተም በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ።

**አማኞችን ድፍረትን በመስጠት ይሞላቸዋል።**

የሐዋርያት ሥራ ፬ ፡ ፴፩

ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ ።

**እርሱ መለኮታዊውን ፍቅር እንዲሠራ ያደርጋል ።**

ሮሜ ፭ ፡ ፭

በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም ።

የሐዋርያት ሥራ ፩ ፡ ፰

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፡ በኢየሩሳሌም .... እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ... ።

## ፲፩. የእግዚአብሔር ችሎታ

ዕብራውያን ፯ ፡ ፳፭
ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብ ሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል ።

ይሁዳ ፳፬
ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆ ማችሁ ለሚችለው ፤

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፲፪
... ያመንሁትን አውቃለሁና የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፱ ፡ ፰
እግዚአብሔር ሁልጊዜ በነገር ሁሉ ትበዙ ዘንድ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል ።

ሉቃስ ፫ ፡ ፰
ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያ ስነሣለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና ።

ሮሜ ፬ ፡ ፲፱ ፤ ፳ ና ፳፩
... አብርሃም ለእግዚአብሔርም ክብር እየ ሰጠ ፡ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲ ችል አጥብቆ እየተረዳ ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም ።

## ፲፰. የእግዚአብሔር ችሎታ

ፊልጵስዮስ ፫ ፡ ፳፩
... እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት ፣ ....

ዳንኤል ፬ ፡ ፴፯
አሁንም እኔ ናቡከደነፆር የሰማይን ንጉሥ አመሰግናለሁ ፣ ታላቅም አደርገዋለሁ ፣ አከብረውማለሁ ። ሥራው ሁሉ እውነት መንገዱም ፍርድ ነውና ፣ በትዕቢትም የሚሄዱትን ያዋርድ ዘንድ ይችላልና ።

ዳንኤል ፫ ፡ ፲፯ ፣ ፳፮ ና ፳፯
የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል ፣ ከእጅህም ያድነናል ፣ ንጉሥ ሆይ ! ... የዚያን ጊዜም ናቡከደነፆር ወደሚነድደው ወደ እሳቱ እቶን በር ቀርቦ፡— እናንተ የልዑል አምላክ ባሪያዎች ፣ ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም ፣ ኑ ውጡ ብሎ ተናገራቸው ። ..... እሳቱም በእነዚያ ሰዎች አካል ላይ ኃይል እንዳልነበረው ፣ የራሳቸውም ጠጉር እንዳልተቃጠለች ... የእሳቱም ሽታ እንዳልደረሰባቸው አየ ።

ዕብራውያን ፪ ፡ ፲፰
እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና ።

### በሞት ላይ ኃይል

ዕብራውያን ፲፩ ፡ ፲፱
እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንዲቻለው አሰቦአልና ፣ .....

## ፲፮. የእግዚአብሔር ችሎታ

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፡ ፲፭

ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል ።

ሮሜ ፲፬ ፡ ፬

አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል ።

ኤፌሶን ፫ ፡ ፳ና ፳፩

እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው ለእርሱ በቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ እስከ ዘላለም ክብር ይሁን ፤ አሜን ።

የሐዋርያት ሥራ ፳ ፡ ፴፪

አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ ።

ሮሜ ፲፩ ፡ ፩ ና ፳፫

እንግዲህ ፡—እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን? እላለሁ ። አይደለም ፤ እኔ ደግሞ እስራኤላዊና ከአብርሃም ዘር ከብንያምም ወገን ነኝና ።...
እነዚያም ደግሞ በአለማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ በዛፉ ውስጥ ይገባሉ ፤ እግዚአብሔር መልሶ ሊያገባቸው ይችላልና ።

## ፲፯. ኃጢአትን ይቅር የሚል የክርስቶስ ኃይል

መዝሙር ፻፳፱ ፡ ፫ ና ፬

አቤቱ ፥ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ ፥ አቤቱ ማን ይቆማል ? ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና ።

፪ኛ ዜና መዋዕል ፯ ፡ ፲፬

በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ ፣ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ ።

ማርቆስ ፪ ፡ ፱—፲፪

ሽባውን ፡— ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ ፡— ተነሣ አልጋህንም ተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል? ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ሽባውን ፡—አንተን እልሃለሁ ፥ ተነሣ ፥ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው ። ተነሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ ፡ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና .... እግዚአብሔርን አከበሩ ።

ሉቃስ ፲፪ ፡ ፲

በሰው ልጅም ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል ፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ ግን አይሰረይለትም ።

## ፲፰. ነፍስን የሚፈውስ የክርስቶስ ኃይል

፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፡ ፲፯

ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥ
ረት ነው ፤ አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም
አዲስ ሆኖአል ።

ዮሐንስ ፲፩ ፡ ፳፮

ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ፤ ሕያው የሆ
ነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ፤
ይህን ታምኛለሽን ? አላት ።

ዕብራውያን ፭ ፡ ፱

ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክ
ንያት ሆነላቸው ።

ሮሜ ፭ ፡ ፳፩

ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ ፥ እንዲሁም
ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ
ይነግሥ ዘንድ ፥ ጸጋ ከመጠን በላይ በለጠ ።

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፲

አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ መገለጥ ታይቶአል ። እርሱ ሞትን ሽሮአልና...
በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን
አውጥቶአል ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፡ ፲፩

የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን
ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥ
ጋችን ተሸክመን እንዞራለን ።

ዮሐንስ ፲ ፡ ፲

ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ
ስለ ሌላ አይመጣም ፥ እኔ ሕይወት ... እንዲበዛ
ላችሁ መጣሁ ።

## ፲፱. አካልን የሚፈውስ የክርስቶስ ኃይል

ሉቃስ ፭ ፡ ፲፯

አንድ ቀንም ያስተምር ነበር ፤ ከገሊላና ከይሁዳ መንደሮችም ሁሉ ከኢየሩሳሌምም መጥተው የነበሩ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ይቀመጡ ነበር ፤ እርሱም እንዲፈውስ የጌታ ኃይል ሆነለት ።

ሉቃስ ፰ ፡ ፵፫ ና ፵፬

ከአሥራ ሁለት ዓመትም ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት ነበረች ፥ ትዳርዋንም ሁሉ ለባለመድኃኒቶች ከስራ ማንም ሊፈውሳት አልተቻለውም ። በኋላውም ቀርባ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች ፥ የደምዋም ፈሳሽ በዚያን ጊዜ ቆመ ።

ማርቆስ ፮ ፡ ፶፮

በገባበትም ሥፍራ ሁሉ መንደርም ከተማም ገጠርም ቢሆን በገበያ ድውዮችን ያኖሩ ነበር የልብሱንም ጫፍ እንኳ ሊዳስሱ ይለምኑት ነበር የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ ።

ማቴዎስ ፰ ፡ ፲፮ ና ፲፯

በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ በነቢዩ በኢሳይያስ ፦— እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ መናፍስትን በቃሉ አወጣ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ ።

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፯

እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና ።

## ፳. ማንኛውንም ሕመም የሚፈውስ ኃይል

ማቴዎስ ፰ ፡ ፫

እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና ፡— እወዳለሁ ንጻ አለው ። ወዲያውም ለምጹ ነጻ ።

ሉቃስ ፲፫ ፡ ፲፫

እጁንም ጫነባት ፤ ያን ጊዜም ቀጥ አለች ፣ እግዚአብሔርንም አመሰገነች ።

ሉቃስ ፯ ፡ ፳፩

በዚያች ሰዓት ከደዌና ከሥቃይ ከክፉዎች መናፍስትም ብዙዎችን ፈወሰ ፣ ለብዙ ዕውሮችም ማየትን ሰጠ ።

ሉቃስ ፲፯ ፡ ፲፪ ና ፲፬

ወደ አንዲት መንደርም ሲገባ በሩቅ የቆሙት አሥር ለምጻሞች ተገናኙት ፤ ... አይቶም ፡— ሂዱ ፣ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ አላቸው ። እነሆም ሲሄዱ ነጹ ።

ማቴዎስ ፰ ፡ ፲፬ ና ፲፭

ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት ገብቶ አማቱን በንዳድ ታማ ተኝታ አያት ፣ እጅዋንም ዳሰሰ ፣ ንዳዱም ለቀቃት ተነሥታም አገለገለቻቸው ።

ሉቃስ ፳፪ ፡ ፶ ና ፶፩

ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው ። ኢየሱስ ግን ... ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው ።

## ፳፩ኛ. ማንኛውንም ሕመም የሚፈውስ ኃይል

ማቴዎስ ፱ ፡ ፳፰—፴

ወደ ቤትም በገባ ጊዜ ዕውሮቹ ወደ እርሱ ቀረቡ ፥ ኢየሱስም ፡—ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁ ን? አላቸው ። አዎን ጌታ ሆይ አሉት ። በዚያን ጊዜ፡— እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ ። ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ ።..

ማቴዎስ ፲፪ ፡ ፲፫

ከዚያም በኋላ ሰውየውን ፡ እጅህን ዘርጋ አለው ። ዘረጋትም እንደ ሁለተኛይቱም ደህና ሆነች ።

ማቴዎስ ፰ ፡ ፭—፯ ና ፲፫

ወደ ቅፍርናሆምም በገባ ጊዜ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ፡— ጌታ ሆይ ፥ ብላቴናዬ ሽባ ሆኖ እጅግ እየተሣቀየ በቤት ተኝቶአል ብሎ ለመነው ። ... ኢየሱስም ለመቶ አለቃው ፡—ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው ። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ ።

ዮሐንስ ፭ ፡ ፭ ፤ ፰ ና ፱

በዚያም ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ ፤ ... ኢየሱስ ፡— ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው ። ወዲያውም ሰውዬው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ ያም ቀን ሰንበት ነበረ ።

## ፳፬. ኢየሱስ የማይፈውሰው ምንም ዓይነት በሽታ የለም ።

ያዕቆብ ፭ ፡ ፲፬ ና ፲፭

ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ ፤ ... የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ፥ ጌታም ያስነሣዋል ፤ ....

ማቴዎስ ፬ ፡ ፳፫

ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር ።

ሉቃስ ፮ ፡ ፲፯—፲፱

.... ከደዌያቸው ሊፈወሱ ... ከርኩሳንም መናፍስት ይሣቀዩ የነበሩት ተፈወሱ ፤ ከእርሱም ኃይል ወጥቶ ሁሉን ይፈውስ ነበርና ሕዝቡ ሁሉ ሊዳስሱት ይሹ ነበር ።

ማቴዎስ ፲፬ ፡ ፴፮

የልብሱንም ጫፍ ብቻ ሊዳስሱ ይለምኑት ነበር የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ ።

ማቴዎስ ፲፭ ፡ ፴

ብዙ ሕዝብም አንካሶችን ፥ ዕውሮችንም ብዙ ይዘው ወደ እርሱ ቀረቡ ፥ በኢየሱስም እግር አጠገብ ጣሉአቸው ፤ ፈወሳቸውም ፤

ማቴዎስ ፲፱ ፡ ፪

ብዙ ሕዝብም ተከተሉት በዚያም ፈወሳቸው።

## ፳፫. አጋንንትን የሚያስወጣ የክርስቶስ ኃይል

ማቴዎስ ፲፯ ፡ ፲፰

ኢየሱስም ገሠጸው ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ ፤ ብላቴናውም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ ።

ሉቃስ ፬ ፡ ፵፩

አጋንንትም ደግሞ ፡— አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉ እየጮኹም ከብዙዎች ይወጡ ነበር ፤ ገሠጻቸውም ክርስቶስም እንደ ሆነ አውቀውት ነበርና እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም።

ማቴዎስ ፰ ፡ ፳፰—፴፪

ወደ ማዶም ወደ ጌርጌሴኖን አገር በመጣ ጊዜ ፥ አጋንንት ያደረባቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ወጥተው ተገናኙት ፤ እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ እጅግ ክፉዎች ነበሩ ። እነሆም ፡—ኢየሱስ ሆይ ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቅየን ወደዚህ መጣህን ? እያሉ ጮኹ ። ከእነርሱም ርቆ የብዙ እርያ መንጋ ይሰማራ ነበር ። አጋንንቱም ፡—ታወጣንስ እንደሆንህ ፥ ወደ እሪያው መንጋ ስደደን ብለው ለመኑት ። ሂዱ አላቸው።

ማቴዎስ ፲፪ ፡ ፳፪

ከዚህም በኋላ ጋኔን ያደረበትን ዕውር ዲዳም ወደ እርሱ አመጡ ዕውሩም ዲዳውም እስኪያይና እስኪናገር ድረስ ፈወሰው ።

## ፳፬. ሙት የሚያስነሣ የክርስቶስ ኃይል

ሉቃስ ፯ ፡ ፲፬ ና ፲፭

ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ ፥ የተሸከሙትም ቆሙ ፤
አለውም ፡— አንተ ጐበዝ ፥ እልሃለሁ ፥ ተነሣ ።
የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ ፥
ለእናቱም ሰጣት ።

ዮሐንስ ፲፩ ፡ ፳፫—፳፭ ና ፵፫ ና ፵፬

ኢየሱስም ፡—ወንድምሽ ይነሣል አላት ።
ማርታም ፡—በመጨረሻ ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ
አውቃለሁ አለችው ። ኢየሱስም ፡— ትንሣኤና
ሕይወት እኔ ነኝ ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው
ይሆናል ፤ ... ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ ፡— ዓል
ዓዛር ሆይ ፥ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ ። የሞተውም
እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ ፤
ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበረ ።
ኢየሱስም ፡— ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው ።

ሉቃስ ፰ ፡ ፵፱ ፤ ፶፬ ና ፶፭

እርሱም ገና ሲናገር አንድ ሰው ከምኵራብ
አለቃው ቤት መጥቶ ፡— ልጅህ ሞታለች ፥ እንግ
ዲህ መምህሩን አታድክም አለ ። ... እርሱ ግን
እጅዋን ይዞ ፡— አንቺ ብላቴና ፥ ተነሺ ብሎ ጮኸ።
ነፍስዋም ተመለሰች ፥ ፈጥናም ቆመች ፥ ...

## ፳፫· የእግዚአብሔር የትንሣኤ ተስፋ

ዮሐንስ ፭ ፡ ፳፭
እውነት እውነት እላችኋለሁ ፤ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው ፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ ።

ዮሐንስ ፮ ፡ ፵
ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው ፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ።

ዮሐንስ ፭ ፡ ፳፰ ና ፳፱
በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል ፤ ... ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ ።

የሐዋርያት ሥራ ፳፬ ፡ ፲፭
ጻድቃንም ዓመፀኞችም ከሙታን ይነሡ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፡ ፲፬
ጌታን ኢየሱስን ያስነሣው እኛን ደግሞ ከኢየሱስ ጋር እንዲያስነሣን ከእናንተም ጋር እንዲያቀርበን እናውቃለንና ።

፩ኛ ተሰሎንቄ ፬ ፡ ፲፮
ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ።

## ፳፮. የማይወሰነው የክርስቶስ ኃይል

ማቴዎስ ፳፰ ፡ ፲፰

ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ፡— ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ ።

ሮሜ ፩ ፡ ፳

የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና ፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ ።

፩ኛ ጴጥሮስ ፫ ፡ ፳፪

እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ ።

ዮሐንስ ፫ ፡ ፴፩

ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው ፥ ከምድርም የሚሆነው የምድር ነው የምድሩንም ይናገራል ። ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው ።

ራዕይ ፫ ፡ ፯

... የዳዊት መክፈቻ ያለው የሚከፍት የሚዘጋም የሌለ የሚዘጋ ፥ የሚከፍትም የሌለ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው እርሱ እንዲህ ይላል ፡—

፪ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፫

የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን ፥ ...

## ፳፺. የማይወሰነው የክርስቶስ ኃይል

### ሁሉን ነገር ለማወቅ

ማቴዎስ ፲፯ ፡ ፳፯

ነገር ግን እንዳናሰናክላቸው ወደ ባሕር ሂድና መቃጥን ጣል ፣ መጀመሪያ የሚወጣውን ዓሣ ውሰድና አፉን ስትከፍት ገንዘብ ታገኛለህ ፡ ያን ወስደህ ስለ እኔና ስለ አንተ ስጣቸው አለው ።

ዮሐንስ ፪ ፡ ፳፭

ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና ።

ሮሜ ፪ ፡ ፲፮

... በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳ ስተማርሁ በሰው ዘንድ የተሰወረውን በሚፈርድ በት ቀን ይሆናል ።

### አምስት ሺህ በተአምር መመገብ

ማቴዎስ ፲፬ ፡ ፲፯—፳፩

እነርሱም ፡— ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር በዚህ የለንም አሉት ። እርሱም ፡— እነዚያን ወደዚህ አምጡልኝ አላቸው ። ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ ፣ አምስቱንም እንጀ ራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ ፣ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ፣ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ ። ሁሉም በል ተው ጠገቡ ፣ የተረፈውንም ቁርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ ። ... የበሉት አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር ።

## ፳፰. የማይወሰነው የክርስቶስ ኃይል

### በውኃ ላይ መራመድ

ማቴዎስ ፲፬ ፡ ፳፭

ከሌሊቱም በአራተኛው ክፍል ኢየሱስ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ ።

### ዝናብን ሁሉ ማቆም

ራዕይ ፲፩ ፡ ፮

እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው ፤ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው ።

### ማዕበልንና ባሕርን ጸጥ ማድረግ

ማቴዎር ፰ ፡ ፳፮

እርሱም ፡— እናንተ እምነት የጐደላችሁ ፤ ስለ ምን ትፈራላችሁ ? አላቸው ፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ ፤ ታላቅ ጸጥታም ሆነ ።

### በግድግዳ ውስጥ ማለፍ

ዮሐንስ ፳ ፡ ፳፮

ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ ፤ በመካከላቸውም ቆሞ ፡— ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው ።

### ምድርን በአንድ ላይ መያዝ

ቆላስይስ ፩ ፡ ፲፮ ና ፲፯

... ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል ።

## ፳፱. የማይወሰነው የክርስቶስ ኃይል

ሮሜ ፮ ፡ ፱

ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና ።

ሮሜ ፰ ፡ ፲፩

ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል ።

ራዕይ ፩ ፡ ፲፰

... ሕያው እኔ ነኝ ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥

መዝሙር ፷፮ ፡ ፩—፬

በምድር ያላችሁ ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ ፥ ለስሙም ዘምሩ ፥ ለምስጋናውም ክብርን ስጡ ። እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ፡— ሥራህ ግሩም ነው ፤ ኃይልህ ብዙ ሲሆን ጠላቶች ዋሹብህ ። በምድር ያሉ ሁሉ ለአንተ ይሰግዳሉ ፥ ለአንተም ይዘምራሉ ፥ ለስምህም ይዘምራሉ ።

### በግዛቱ ውስጥ ያለ ኃይል

፩ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፡ ፳

የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና ።

ራዕይ ፲፯ ፡ ፲፬

እነዚህ በጉን ይወጋሉ በጉም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለሆነ እነርሱን ድል ይነሣል ፥.

## ፴. የማይወሰነው የክርስቶስ ኃይል

### ከሕይወት ሁሉ በላይ

ዮሐንስ ፲፯ ፡ ፪

በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠኸው ፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ .....

### እርሱ ሲሞት መሬት ተናወጠች ።

ማቴዎስ ፳፯ ፥ ፶ ና ፶፩

ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ ። ... ምድርም ተናወጠች ።

### የራሱን ሕይወት እንደገና ማስነሣት

ዮሐንስ ፲ ፡ ፲፯ ና ፲፰

ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለ ዚህ አብ ይወደኛል ። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም ። ላኖራት ሥል

ጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህ ችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ ።

### ሰማያዊ ክብሩን ማንፀባረቅ

ማቴዎስ ፲፯ ፡ ፪

በፊታቸውም ተለወጠ ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ ።

### በኃይልና በክብር መመለስ

ማቴዎስ ፳፮ ፡ ፷፬

ኢየሱስም ፡— አንተ አልህ ነገር ግን እላች ኋለሁ ፥ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላ ችሁ አለው ።

## ፴፩. የማይወሰነው የክርስቶስ ኃይል

### ኃጢአትን ይቅር ለማለት

ማቴዎስ ፱ ፡ ፮

ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአትን ያስተሰርይ ዘንድ የሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ በዚያን ጊዜ ሽባውን ፦ ተነሣ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው ።

### የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት

ዮሐንስ ፲ ፡ ፳፯ ና ፳፰

በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል ፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ ፥ .....

### ማንኛውንም ለማዳን

ሉቃስ ፳፬ ፡ ፵፯

በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ......

### ነፍሳትን ለማንጻት

፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፪

በመንፈስም እንደሚቀደሱ ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ .....

### አሸናፊ ለማድረግ

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፬ ፡ ፲፰

ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል ፤ ....

### በእምነት ለመጠበቅ

፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፡ ፭

እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ፥ ....

## ፴፪. የክርስቶስ የስሙ ኃይል

ፊልጵስዩስ ፪ ፡ ፱ ና ፲

በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው ፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለ ውን ስም ሰጠው ፤ ይህም በሰማይና በምድር ከም ድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ ።

ዮሐንስ ፳ ፡ ፴፩

ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአ ብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል ።

ማርቆስ ፱ ፡ ፴፰ ና ፴፱

... መምህር ሆይ ፣ አንድ ሰው በስምህ አጋ ንንትን ሲያወጣ አየነው ፣ ስለማይከተለንም ከለ ከልነው አለው ። ኢየሱስ ግን አለ ፡— በስሜ ተአ ምር ሠርቶ በቶሎ በእኔ ላይ ክፉ መናገር የሚ ችል ማንም የለምና አትከልክሉት ።

ዮሐንስ ፲፬ ፡ ፲፫

... በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋ ለሁ ።

የሐዋርያት ሥራ ፫ ፡ ፮ ና ፯

ጴጥሮስ ግን ፡— ብርና ወርቅ የለኝም ፤ ይህን እሰጥሃለሁ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው ። በቀኝ እጁም ይዞ አስ ነሣው ፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቁርጭምጭምቱ ጸና ። .......

## ፴፫. የክርስቶስ የሞቱ ደም ኃይል

ኤፌሶን ፩ ፡ ፯
… እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላ ችን ስርየት ።

ሉቃስ ፳፪ ፡ ፳
… ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው ።

ራዕይ ፲፪ ፡ ፲፩
እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸው ቃል የተነሣ ድል ነሡት ፣ …

ዕብራውያን ፲፫ ፡ ፳ ና ፳፩
በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስ ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ ፣ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን አሜን ።

ራዕይ ፯ ፡ ፲፬
እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ፣ ልብ ሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ ።

፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፡ ፯
ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን ፣ የል ጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነ ጻናል ።

## ፴፬. ስለ ኃይሉ እግዚአብሔር ይመስገን !

ራዕይ ፭ ፡ ፲፪

በታላቅም ድምፅ ፡— የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ ።

መዝሙር ፻፪ ፡ ፲፭ ና ፲፰

አቤቱ ፡ አሕዛብ ስምህን ፥ ነገሥታትም ሁሉ ክብርህን ይፈራሉ ፤ ... የሚፈጠርም ሕዝብ ለእግዚአብሔር እልል ይላል ።

፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፱

እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ ፥ የንጉሥ ካህናት ፥ ቅዱስ ሕዝብ ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ ።

መዝሙር ፱ ፡ ፲፩

በጽዮን ለሚኖር ለእግዚአብሔር ዘምሩ ፥ በአሕዛብም መካከል አደራረጉን ንገሩ ።

መዝሙር ፳፩ ፡ ፳፫

እግዚአብሔርን የምትፈሩ ፥ አመስግኑት ፤...

መዝሙር ፷፯ ፡ ፭—፯

አቤቱ ፥ አሕዛብ ያመስግኑህ ፥ አሕዛብ ሁሉ ያመስግኑህ ። ምድር ፍሬዋን ሰጠች ፤ እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል ። እግዚአብሔር ይባርከናል ፥ የምድርም ዳርቻ ሁሉ ይፈሩታል ።

## ፴፰. የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረኝ ምን ላድርግ ?

ማቴዎስ ፲፱ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯—፳፩

... መምህር ሆይ ፥ የዘላለምን ሕይወት እን ዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ ? አለው ። እርሱም ፦ ... መልካም የሆነ አንድ ነው ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው ። እርሱም ፦ የትኞቹን ? አለው ። ኢየሱ ስም ፦ አትግደል ፥ አታመንዝር ፥ አትስረቅ ፥ በሐ ሰት አትመስክር ፥ አባትህንና እናትህን አክብር ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው ። ጐበ ዙም ፦ ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄ አለሁ ፤ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው ? አለው። ኢየሱስም ፦ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው ።

ተናዘዝ እመን ፥ ተቀበል

ማርቆስ ፩ ፡ ፲፬ ና ፲፭

... ኢየሱስ ... ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብ ሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌ ልም እመኑ እያለ ... መጣ ።

ዮሐንስ ፩ ፲ ና ፲፪

በዓለም ነበረ ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ ፥ ዓለ ሙም አላወቀውም ። ... ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ።

## ፴፮. ክርስቶስ መንገድ፥ እውነት ፥ ሕይወት ፥ ነው ።

ዮሐንስ ፩ ፡ ፲፯

ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ ።

ዮሐንስ ፲፬ ፡ ፮

ኢየሱስም ፡— እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ።

፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፡ ፳፪

ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው ? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው ።

ማቴዎስ ፯ ፡ ፲፫ ና ፲፬

በጠበበው ደጅ ግቡ ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው ። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው ።

ዮሐንስ ፩ ፡ ፬

በእርሱ ሕይወት ነበረች ፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች ።

ዮሐንስ ፭ ፡ ፳፮

አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና ።

ዮሐንስ ፮ ፥ ፶፩

ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል ፤ ...

## ፴፮. ክርስቶስ ብቻ የደኅንነት ኃይል ነው።

ዕብራውያን ፱ ፡ ፳፬—፳፰

ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሠራች ቅድስት አል ገባምና ፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ ወደ ሰማይ ገባ። ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ ፥ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም ፤ እንዲህ ቢሆንስ ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር ፥ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል ። ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው ፥ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ፥ የብዙ ዎችን ኀጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል ።

### ወደ ሰማይ የሚወስደው ኃይሉ

የሐዋርያት ሥራ ፬ ፡ ፲፪

መዳንም በሌላ በማንም የለም ፥ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና ።

### ወደ ሲኦል የሚጥለው ኃይሉ

ማቴዎስ ፲ ፡ ፳፰

ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋ ንም በገሃነም ሊያጠፉ የሚቻለውን ፍሩ ።

## ፴፰. የክርስቶስ ኃይል እስከመጨረሻ ድረስ ያድናል ።

፩ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፲፭
ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው ፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ ።

ሮሜ ፩ ፡ ፲፮
በወንጌል አላፍርምና ... ለሚያምኑ ሁሉ የእ ግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና ።

ዮሐንስ ፬ ፡ ፲፬
እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም ፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ.... ።

ሮሜ ፫ ፡ ፳፬ ና ፳፭
በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ ። እርሱንም እግዚ አብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስ ተስረያ አድርጎ አቆመው ፤ ይህም በፊት የተደ ረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው ፡ ...

፪ኛ «ጴጥሮስ ፩ ፡ ፲
ስለዚህ ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና ።

ሉቃስ ፲ ፡ ፲፱
እነሆ ... በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥል ጣን ሰጥቻችኋለሁ ፥ ....

፴፱. ደኅንነት ቀላል ነገር አይደለም ነገር ግን በነፃ ነው ።

## ከዚህ የበለጠ እግዚአብሔርን ያስከፍለ ውም !

ዮሐንስ ፫ ፡ ፲፮

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አን ድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ።

ደኅንነትን ወደ ሰው ያመጣ ጸጋ ። የፍጡር ሁሉ ጌታ ለእኛ ሁሉ የሞተው !

ሉቃስ ፳፫ ፡ ፴፬ ና ፵፮

ኢየሱስም ፡— አባት ሆይ ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ ። ... ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ፡— አባት ሆይ ነፍሴን በእ ጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ ። ይህንም ብሎ ነፍ ሱን ሰጠ ።

እኛ ግን በነፃ መውሰድ ይቻለናል ።

ራዕይ ፳፪ ፡ ፲፯

መንፈሱና ሙሽራይቱም ፡— ና ይላሉ ። የሚ ሰማም ፡— ና ይበል ። የተጠማም ይምጣ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ ።

አብ የዋጃቸውን ሙሽራ ልጆቹን እንደሚወድ ይወዳታል ፡— ከዚህ የበለጠ ፍቅር የለም !

ዮሐንስ ፲፯ ፡ ፳፫

እኔም በእነርሱ አንተም ፡— በእኔ ስትሆን በአ ንድ ፍጹማን እንዲሆኑ ፥ ... እንዲሁም ዓለም አንተ እንደላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል ።

፵. በኃጢአትህ ተናዘዝና ንስሐ ግባ ።

፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፡ ፱
በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፅም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው ።

የሐዋርያት ሥራ ፫ ፡ ፲፱
... ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም ።

በእግዚአብሔር ልጅ እመን ።
፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፡ ፲፩ ና ፲፪
እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው ። ልጁ ያለው ሕይወት አለው ፤ የእግዚአብ ሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም ።

ዮሐንስ ፫ ፡ ፴፮
በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእ ርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም ።

ሮሜ ፮ ፡ ፲፮
ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያ ዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን ? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ ።

ሮሜ ፮ ፡ ፲፫
ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድር ጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ ፣ ነገር ግን ... ራሳ ችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ ።

## ፵፩. የእግዚአብሔር ኃይል በእውነተኞች አማኞች ውስጥ

### በፍርሃት ፈንታ ፍቅር

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፯

እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና ።

፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፡ ፲፰

ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም ፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና ፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።

### በጥላቻ ፋንታ ፍቅር

፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፡ ፳ ና ፳፩

ማንም ፡— እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው ፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል ? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን ።

ገላቲያ ፭ ፡ ፳፪ ና ፳፫

የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር ፥ ደስታ ፥ ሰላም ፥ ትዕግሥት ፥ ቸርነት ፥ በጎነት ፥ እምነት ፥ የውሃት ፥ ራስን መግዛት ነው ። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም ።

### በጥርጥር ፈንታ እምነት

ሮሜ ፰ ፡ ፴፭ ና ፴፯

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ? መከራ ወይስ ጭንቀት ፥ ወይስ ስደት ፥ ወይስ ራብ ፥ ወይስ ራቁትነት ፥ ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ።

## ፵፱. የእግዚአብሔር ኃይል በእውነተኞች አማኞች ውስጥ

### ፍቅር እንጂ ብቸኝነት የለም ።

ዕብራውያን ፲፫ ፡ ፭

አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን ፥ ያላችሁም ይብቃችሁ ፤ እርሱ ራሱ ፦— አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና ።

### በስቃይ ፈንታ ሰላም

ዮሐንስ ፲፬ ፡ ፳፯

ሰላምን እተውላችኋለሁ ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም ። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም ።

ሮሜ ፰ ፡ ፮

ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው ።

ሮሜ ፭ ፡ ፩

እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ ።

### እውነተኛ ብልጽግና እንጂ ስግብግብነት የለም ።

ሉቃስ ፲፪ ፡ ፲፭

የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ፥ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ አላቸው ።

ያዕቆብ ፪ ፡ ፭

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ፥ ስሙ ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለ ጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?

## ፵፫. የእግዚአብሔር ኃይል በእውነተኞች አማኞች ውስጥ

እርግጠኛነት እንጂ አጠራጣሪነት የለም ።

፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፡ ፲፫
የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌ ላችኋለሁ ።

በርኩሰት ፋንታ ንጽህና

፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፳፪
ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ ።

፩ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፭
የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው ።

በኃዘን ፈንታ መለኰታዊ ደስታ

ሮሜ ፲፭ ፡ ፲፫
የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላ ምን ሁሉ ይሙላባችሁ ።

ዮሐንስ ፲፭ ፡ ፲፩
ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ ።

ዮሐንስ ፲፮ ፡ ፳፪
እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ ፤ ነገር ግን እንደ ገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል ፡ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም ።

## ፵፩. የእግዚአብሔር ኃይል በእውነተኞች አማኞች ውስጥ

### በድካም ፈንታ ብርታት

ኤፌሶን ፮ ፥ ፲

በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ ።

### በተስፋቢስነት ፈንታ ተስፋ

ቲቶ ፪ ፥ ፲፫

የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን ....

ዕብራውያን ፮ ፥ ፲፰ ና ፲፱

እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይችል በሁለት በማይለወጥ ነገር ፥ በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ ፥ በመሐላ በመካከል ገባ ፤ ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው ።

፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፲፪

ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ ፥ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር በሚጐበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን ።

### በውሸት ፈንታ እውነት

ዮሐንስ ፰ ፥ ፴፪

እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል ... ።

## ፵፫. የእግዚአብሔር ኃይል በእውነተኞች አማኞች ውስጥ

### በመሸነፍ ፈንታ ማሸነፍ

፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፡ ፬

ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸ ንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።

ራዕይ ፲፭ ፡ ፪

በእሳትም የተቀላቀለውን የብርጭቆ ባሕር የሚመስለውን አየሁ ፣ በአውሬውና በምስሉም በስሙም ቁጥር ላይ ድል ነሥተው የነበሩት የእግ ዚአብሔርን በገና ይዘው በብርጭቆ ባሕር ላይ ሲቆሙ አየሁ ።

### በሕፃንነት ፈንታ እድገት

ዕብራውያን ፮ ፡ ፩

ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚ ናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠ ረትን ደግመን አንመሥርት ፣ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው ።

፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፪

በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።

ኤፌሶን ፬ ፡ ፲፭

ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ ።

### ክርስቶስን መምሰል

፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፡ ፮

በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደ ተመ ላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል ።

## ፵፮. የእግዚአብሔር ኃይል በእውነተኞች አማኞች ውስጥ

### ለውስጥ ሰውነት የሚሰጥ ጥንካሬ

ኤፌሶን ፫ ፡ ፲፮
በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እን ድትጠነክሩ ... እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ ።

ፊልጵስዮስ ፬ ፡ ፲፫
ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እች ላለሁ ·።

### በሰው ጥበብ አለመታመን

፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፡ ፬
ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመ ግለጥ ነበረ እንጂ ፣ በሚያባብል በጥበብ ቃል አል ነበረም ።

### የመመስከር ኃይል

የሐዋርያት ሥራ ፩ ፡ ፰
ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወ ረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፣ በኢየሩሳሌም .... እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆና ላችሁ ... ።

የሐዋርያት ሥራ ፭ ፡ ፴፪
እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ፣ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው ።

የሐዋርያት ሥራ ፬ ፡ ፴፫
ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር ፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው ።

## ፵፯. አማኞችን የሚጠብቅ የእግዚአብሔር ኃይል

ዮሐንስ ፲፯ ፡ ፲፭

ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እን ድታወጣቸው አልለምንም ።

ፊልጵስዮስ ፬ ፡ ፯

አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል ።

ሉቃስ ፲ ፡ ፲፰ ና ፲፱

እንዲህም አላቸው ፤ ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ ። እነሆ ፤ እባቡንና ጊን ጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ ፤ የሚጐዳችሁም ምንም የለም ።

ራዕይ ፫ ፡ ፲

የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ ፤ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብ ቅሃለሁ ።

ራዕይ ፪ ፡ ፳፮

ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ... በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ ።

ኤፌሶን ፮ ፡ ፲ ና ፲፩

.... በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ ። የዲያቢሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እን ዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።

## ፵፰. የእግዚአብሔር አጠቃላይ ተስፋ

የእኛን እምነት የሚያሟላው ያልተወሰ ነው አምላክ ብቻ ነው ።

ማቴዎስ ፳፩ ፡ ፳፪
አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀ በላላችሁ ... ።

ዮሐንስ ፲፭ ፡ ፯ ና ፰
በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል ። ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል ።

፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፡ ፲፬ ና ፲፭
በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው ፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል ። የምን ለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።

ማቴዎስ ፯ ፡ ፯ ና ፰
ለምኑ ፥ ይሰጣችሁማል ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል ። የሚለ ምነው ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል ።

ዮሐንስ ፲፬ ፡ ፲፪—፲፬
እውነት እውነት እላችኋለሁ ፥ በእኔ የሚያ ምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደር ጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል ፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ ።

ማርቆስ ፲፩ ፡ ፳፬
ስለዚህ እላችኋለሁ ፤ የጸለያችሁትን የለመና ችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ ፤ ይሆንላ ችሁማል ።

መዝሙር ፴፯ ፡ ፬ ና ፭
በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ ፤ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል ። መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ ፤ በእርሱም ታመን ፤ እርሱም ያደርግ ልሃል ።

ሉቃስ ፲፯ ፡ ፯
ጌታም አለ ፡— የሰናፍጭን ቅንጣት የሚያ ህል እምነት ቢኖራችሁ ፤ ይህን ሾላ ፡— ተነቅለህ ወደ ባሕር ተተከል ብትሉት ይታዘዝላችሁ ነበር ።

ፊልጵስዮስ ፬ ፡ ፲፱
አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክ ብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል ።

፩ኛ ዮሐንስ ፫ ፡ ፳፩ ና ፳፪
ወዳጆች ሆይ ፤ ልባችንስ ባይፈርድብን በእ ግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን ፤ ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለ ሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛ ለን ።

ማርቆስ ፱ ፡ ፳፫
ኢየሱስም ፡— ቢቻልህ ትላለህ ፤ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው ።

የዓለም ሚስዮናውያን ማተሚያ ቤት

Published in numerous languages by World Missionary Press, Inc., as God supplies funds in answer to prayer.
**For questions or more information by country, visit: www.wmp-contacts.org**

Cover photo STSci-PRC2003-11a of Helix Nebula courtesy of NASA and STSci

Read booklets online or by App
www.wmp-readonline.org

World Missionary Press
PO Box 120
New Paris, IN 46553-0120 USA
www.wmpress.org 11-24 717 Amharic POG